# በውሸት ምላስ ሃገር ሲታመስ

ውሸቱ ተጋኖ፣ እውነት ተሸፍኖ፣
እንዲህ ከቀጠለ፣ እንደባህል ሆኖ፤
በቂ ምልክት ነው፣ ለመኖር ተዋርዶ።

ለዚህ ጹሑፍ መነሻ የሆነኝ በቅርቡ በኢትዮጵያ ሳታላይት ቴሌቪዥን (እሳት) ላይ ጋዜጠኛ አበበ ገላው ከአቶ መኮንን ዘለለው ጋር ያደረጉትን ውይይት መሠረት በማድረግ ነው።

አቶ መኮንን ዘለለው ሲሻው ኢህአዴግ ሲመቸው ሕውሃት በሚል መጠሪያ ስም ሃገራችንን ለጥፍት ሕዝቡን ለውርደት ያበቃውን ቡድን ማንነት ፍርጥርጥ አደርገው በማቅረብ ውሸቱን አጋልጠዋል። በእርግጥ ከዚህ በፊት አቶ ገብረመድህን አርአያ ለሃያ ዓመት በመላው ኢትዮጵያ ሰላሳ ሰባት ዓመት በትግራይ ክፍለሃገር 'የትግራይ ሕዝብ ነፃነት ግንባር' በሚል ስም በክፍለሃገሩ ያደረገውን ውንብድናና ዘረፋ ሰፋ ባለው ጹሑፋቸውና በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን ባደረጓቸው ቃል ምልልሶች በማስረጃ በማስደገፍ ስለዚህ ድርጅት ማንነት ገልጸውልናል።
አቶ መኮንን ዘለለው ደግሞ ዘለቅ ብለው የጥፋቱ መልክተኞቹ እነማን እንደሆኑ፤ የጥፋት ተልኮአቸውን፤ የትግራይን ወጣትና ሕዝቡን ልቡን እንዴት እንደሰለቡት አኤውን እንደገደሉት አንድ በአንድ በመዘርዝር በኢትዮጵያ ሳታላይት ቴሌቪዥን (ኢሳት) ከጋዜጠኛ አበበ ገላው ጋር ባደረጉት ውይይት ግልጽ አድርገውታል። በተጨማሪም ይህ ቡድን በ1970ዎቹ በትግራይ ሕዝብ ላይ ይፈጽም ከነበረው ግድያና ሰቆቃ በፍጹም እንዳልተለወጠ ብዙ ማስረጃዎችን በመጥቀስ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ አቅጣጫ የሚያሲዝ ሐቅን የሚያስጨብጥ አንኳር የሆኑ ነጥቦችን ጠቁመዋል።

ለምሳሌ አንድ ወጣት አቶ መኮንን ዘለለው ባሉበት ከመንደሩ ተጠርቶ በኮለኔልነት ማዕረግ ያለው ሳሞራ ዩኑስ አጃቢዎቹ በጥይት ደብድበው እንዲገሉት ያዛል። ወጣቶቹ ሊገሉት ስላልፈለጉ ተኩሰው ይስቱታል። ሳሞራ ዩኑስ ይህን የትግራይ ወጣት ግንባሩን በሽጉጥ ተኩሶ በጥርቆ ከገደለው በኋላ ከወራጁ ወንዝ እንዲጥሉት ያደርጋል። በአሁኑ ወቅት የአማራውና የኦሮሞው የደቡብ ሕዝቦች ተከታዮቻቸው አንዱን የዘር ሐረጋቸውን ተኩሰው ቢስቱት ወዲያውኑ እንደሚገደሉ ስለሚያውቁ ፤ልጆቻቸው፣ እናቶቻቸው፣ አባቶቻቸው፣ ወንድሞቻቸው፣እህቶቻቸው ቢሆኑም ይገድላሉ። በማንኛው መስከ ወያኔን እያገለገሉ ያሉ ድኩማኖችም ያደርጉታል። በዚያን ወቅት ሳሞራ ተኮሰው የሳቱትን ያልገደለ ለበት ምክንያት በሌላ ውቅት የሚያጅቡት እንደሚገድሉት በመፍራት እንጅ አዝኖላቸው አልነበረም። ይሄው ቡድን የትግራይን ወጣቶች 'ባዶ ስድስት' በሚባል ከምድር በታች እስር ቤት አጉሮ ትምህርት ቤት ተልከዋል ብሎ ለሕዝብ የሚናገር ኬሲ ቡድን ነው። የትግራይ ሕዝብ ስለልጆቹ መጥየቁን ሲያቆም ይባስ ብለው በጅምላ ገለዋቸው በደርግ አይሮፕላን ተፈጁ ብለው የሚናገሩ ናቸው። እንግዲህ በደርግ ስም የሐውዜን እልቂት፣ በኦነግ ስም በ1984 ዓ ም ፤ በአርባጉጉ፣በበደኖ፣ በአረካ የተደረጉትን ጭፍጨፋዎች ያጤናሉ። ቢጋንቤላ ፣ በኦጋዴን የተደረጉት ጭፍጨፋዎች ለዓለሙ አቀፍ ፍርድቤት እጩ ያደረጋቸው ወንጀል ነው።

እነዚህ ወንጀለኞች እነማናቸው? መለስ ዜናዊ ፣ ስባት ነጋ፣ ስዩም መስፍ፣ ሳሞራ ዩኑስና አባይ ፀሐዬ ናቸው። ስለነዚህ ገለሰቦች ገጸ ባህሪ በኢትዮጵያ የአሜሪካ ባለሙሉሥልጣን አንባሳደር የነበሩት ዲቪድ ሺል፤ በኢትዮጵያ ሳታላይት ቴሌቪዥን ከጋዜጠኛው አበበ ገላው ጋር ባደረጉት ውይይት እንዲህ ብለዋል፤ 'የኢህአዴግ መንግሥት ከተቃዋሚዎች ጋር ለውይይት የመቅረብ ዕድሉ ኒዮ ሰከንድ (neo second)' ነበር ያሉት። ይህም ማለት 1/1000 000 000=.000 000 001 የጠበበ ነው። እንግዲህ የፖለቲካ ጅርጅቶችም ሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከነዚህ ወንጀላቸው ኢፋ ቢወጣ እንዋረዳለን ከሚሉ ጋራ ለሃያ ዓመት መድከም አልነበረበትም። እድሜ ለአቶ መኮንን ዘለለውና ለአቶ ገብረመድህን አርአያ የነዚህን በምላስ ሃገርን ሊያጠፉ የተዘጋጁ ወራዶች መሆናቸውን ፍንጭ ሰጥተውናል። ጨዋው ሰላም ወዳዱ በባህሉና በሃይማኖቱ ተከብሮ የኖረ ሕዝብ በነዚህ መመራቱ በጣም የሚያሳዝን ነው።ከነዚህ ጋር ተደራድሮ በሃገር ላይ ሰላምን አስፍኖ ዕድገት ለማምጣት መሥራት ዘበት ነው። ነፃ አስተሳሰብ በሌለበት ዕድገት መሻት የዋህነት ነው።

መለስ ዜናዊ የወያኔው (Enver Hohva) ከካድሬነት አሰልጣኝነቱ ሌላ በእያንዳዱ ታጋይ ላይ ስለላ ያካሄድ እንደነበር፤ አቶ መኮንን ዘለለው ምስክር ናቸው። ሻዕቢያን በማውገዛቸው ጥርሱን እንደነከሳባቸው ገልጸዋል። ከጃርባው ሻዕቢያን መከታ አድርጎ ሌሎቹ ላይ ይፎልል እንደነበርና አሁንም አብረውት ያሉ ሁሉ ለቆሙለት አላማና ለትግራይ ሕዝብ ካላቸው ፍቅር ሳይሆን ከፍረሃት መሆኑን በግልጽ የሚያሳይ ነው። ከርሱ በአስተሳሰብ ልቀው የሚገኙትን ጥይት እያጎረሰ ሲገላቸው ሌሎቹን ሲያባርራቸው እያዩ አብረው የተጓዙ ናቸው።የየመኑ አሊ አብደላ ሳሕሊ መውጫ መንገዱን ያመቻቸው ለራሱና ለቤተሰቡ ነው። የመለስ ጄሌዎች ከዚህ መማር ይችሉ ነበር። የመለስ

ዜናዊ ብልጣ ብልጥነት ደግሞ የባሰ ነው። ለጥፋቶች ሁሉ ተጠያቂ አድርጓቸው እንደሚወጣ ከዚሁ መናገር ይቻላል። አህያውን ፈርቶ ዳውላውን ይሉ፤ በግል ያሸማቀቃቸውን መለሰ ዜናዊን ትተው ሻዕቢያን ሲያወግዙ ሲያይ እርሱም ብልጡ ሳይቀድሙኝ ልቅደም ብሎ ሻዕቢያን ሲያወግዝ ይሰማል። ሌላው የጥፋት ቁንጮ ያለርህራሄ የትግራይን ወጣቶች ለሻዕቢያ እየላከ በጦር ሜዳ ያስፈጀ፤ በእስር ቤት አጉሮ እየፈረመ ያስገደል (The death doctor) ተብሎ የሚጠራው ስባት ነጋ ነው።በሃገራቸው መሬት ላይ መጓጓዝ ወንጀል ሆኖባችው መታወቂያ አላሳያቹሁን ብሎ በእስር ቤት አጉሮ 'ትምህርት ቤት ተልከዋል የሚል በልጣጣ ውሸታም ነው።በእርስ ቤት ያጎራቸውን በጅምላ ከገደለ በኋላ ደርግ ነው ብሎ የሚዋሽ የዕንጨት ሽበት ያበቀለ አዛውንት ነኝ ባይ ነው። እውነት ይህ ግለሰብ ሃይማኖቱን አጥባቂ ከሆነው ከትግራይ ሕብረተሰብ የተፈጠረ ነው ? እውነተኛው የሃገሪቱ ሠራዊት በኦሮሞውና በአማራው ቤሔረሰብ ስም ኤርትራንና ትግራይን እንደወረረ ተደርጎ ተገደለ። እሺ ታዲያስ ለትግራይ ነፃነት የቆመው ወጣት ለምን ይሆን መፈጀቱ? ወያኔ በትግራይ ይቀሳቀስ እንደነበረው ይቀሳቀሱ የነበሩት የኦሮሞ ነፃነት ግንባር እስከ 1972 ዓ ም ድረስ አንዲት ነብስ አላጠፉም። በእርግጥ ብዙዎቹ እስከ 1969 ዓ ም ድረስ በደርግ መንግሥት በኢፋ ከሚቀሳቁሱ ድርጅቶች አባል ሆነው በፓለቲካው ተሳትፈዋል። በ1970ዎቹ በሐረር ጨርጨር ተቀሳቅሰው ነበር ጠቅላላ አካሄዳቸው የነበረውን መንግሥት ከሥልጣን ለማውረድ እንጂ አንዱን ቤሔር ከሌላው የሚያለያይ ቅስቀሳ አላደረጉም። የውቅቱ የመሐከለኛ ኮሚቴ አባላት፤ ሊቀመበር የነበረው መገርሣ በሪ ፣ ዶክተር ባሮ ቱምሳ፤ አቦማ ምትኩ፣ አላና፣ ገላሳ ዴቦ፣ ሌንጮ ለታ ዲማ ነገዎ እንደነበሩ በአካባቢው ክፍለሃገር ሆኜ ሁኔታውን እከታተል ነበር። እንኳን ሊያነቁት የሄዱትን ሕዝብ ደም ሊያፈሱ ይቅርና የሌላውን ቤሔረሰብ አባል የሆነ ሰው አንድም አልገደሉም። አማራ የሚል ቅስቀሳ ያደረጉ የነበሩት በሱማሊያ መንግሥት ታጥቀው ኦሮሞ መባልን ክደው በሱማሌ አቦ ስም ይቀሳቀሱ የነበሩ ናቸው። እነርሱም ቢሆኑ አማራ ማለት ክርስቲያ ነው ብለው የሚያምኑ ሰለነበሩ በአማራነት ሰው አልገደሉም። በተጨባጭነት የማስታውሰው በባሌ ክፍለሃገር ሁለት የእህአፓ አባል የነበሩ ወጣቶች አንደኛው የእርሻ ልማት ሰራተኛ ሌላው ተማሪ በነዚህ ሰርጎ ገቦች ተገለዋል። በነርሱ የታረደውን ፊሪዳ በመብላታቸውና ክላሽኮብ ጠብመንጃ አዲስ ስለነበር የተሠራበትን ሃገር ለማወቅ በመሞከራቸው እንደርግ መሪዎች ሃይማኖት የሌላቸው ሰላዮች ናቸው ብለው ነበር የገደሏቸው። እንደወያኔ ሰዎችን መታወቂያ የሚጠይቁም አለነበሩም። ብዙዎቹ የኦነግ መሪዎችም በነዚህ ሠርጎ ገቦች እንደተፈጁ ይነገራል። ሊቀመበሩ መገርሣ በሪ፣ ዶክተር ባሩ ቱምሳ አቦ ምትኩ የማስታውሳቸው ናቸው። ዶክተር ዲማ ነጎ፤ ገላሳ ዴቦ፣ አላና፣ ሌንጮ ለታ በሕይወት መኖራቸውን ያወኩት ወያኔ ሃገራችንን ሲወር በመጋጀነት አብረው በገቡበት ወቅት ነበር። በኦነግ ስም ትልቁ ጭፍጨፋ የፈጸሙት በሱማሌ አባ ሰም ሱማሌያ ያስታጠቀቻቸው የኦሮሞ ቤሔረሰብ እንደነበሩ በትክክልኝነት መናገር ይቻላል። ወያኔ እነርሱን ከኋላቸው እንደ አበያ በሬ በኦጀ እየወጋ እነርሱ ክርስቲያ የሚሉትን ሕዝብ ወያኔ ግን በጅምላ አማራ የሚባለውን እንዲጨፈጭፉ የመሣሪያ ግምጃ ቤቶችን ከፍቶ በሱማሌ አቦነት በሚታወቁት ሕዝብን ያሰፈጀው ወያኔ ነበር።

በአንፃሩ ደግሞ እነሰባት ነጋ ኦነግ የኦሮሞ ሕዝብ ተወካይ ነው ካሉ በኋላ በድርጅቱ ስም በአማራው ላይ ግድያ እየፈጸሙ የኦሮሞ ሕዝብ እንደፈጸመው አድርገው በኢቲቪ ቅስቀሳ ሰሩበት። እንግድህ እነሰባት ነጋ በትግራይ ሕዝብ ላይ የጀመሩትን ቀጥተኛ ግድያ ወደ መሐል ሃገር ሲገቡ እርስ በርሱ ለማፋጀት ቢሞክሩም አልተሳካላቸውም። ይህ ቡድን የቱን ያህል ጸረ ኢትዮጵያ መሆኑን ከትግራይ ሕዝብ በላይ የሚያውቀው አለ ብሎ ለመገመት ያስቸግራል። ሆኖም ግን የተፈለገውን ያህል በትግራይ ሙሑራን ይህን የጥፋት መልክተኛ ቡድን ዕኩይ ሥራ አልተጋለጠም። ሁለተኛው ሰው ሰዩም መስፍን ከባዕድሜ ጦርነት በኋላ በውሸቱ መለሰን ይስተካከለዋለ ተብሎ ይገመታል። በጦር ግንባር ውሎው እንደመለስ አይታማም። ሆኖም ተስፋዬ ግብረ አብ እንደወትሮው ቅጥፈቱ ተራራውን ባቀጠቀጠው መጽሐፉ የሌሎቹን ጅግንነት አሣንሶ የስዩም መስፍንን አጉልቶ ሲያቀርብ ስዩም መስፍንም ያልሆነውን እንደሆነ መቀበሉ የትኑ ያህል ይህ ቡድን የደካሞች ጥርቅም መሆኑን አመልክቷል። ሳሞራ ዮኑስ የመግደሉን ሱስ ይበልጥ አጠንክሮታል። ምርጫ ተጭብርብሯል ብሎ በ1997 ዓ ም ሰልፍ በወጣው በአዲስ አበባ ሕዝብ ላይ የፈጸመው ግድያ አብይ ምስክር ነው።

አባይ ፀሐዬም ቢሆን አነመለስ አድርግ ያሉት ማንኛውን ቁሻሻ ነገር የሚሰራ መሆኑ በዙዎቹ የሚናገሩት ነው። እነዚህ ያሻቸውን ማድረግ የሚችሉ አንዱ ሌላውን ለማረም አኔው የሌላቸው ጥርቅሞች ናቸው። አሁን የምናየውን የውሲብ ተግባር በበረሃ የተካኑት ሰለሆነ ይሄው በሃገራችን ሶዶምነትን እያስፋፉ ነው። የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዘዳን ሽብርተኛን እዋጋለሁ ሲለ የመጀመሪያዎቹ አቤት ጌታዬ ባዮች ሆኑ። ፕሬዘዳንት ባራክ ኦቦማ ሶዶምነትን ለተቀበሎ ሃገሮች የእርዳት እጅ እንዘረጋለን ሲል፤ የሶዶሞችን ጉበኤ በአዲስ አበባ በማዘጋጀት ለሶዶምነት ዝግጁ መሆናቸውን አሣዩ። ሶዶምነትን ተቃውመው ጳፉ ተብለው ጋዜጦኞ እስር እንደሚገቡ ጠበቁ። የቤተክህነት ሰዎችም እስር ቤቱን እንደሚያጣብቡ ገምቱ። ሶዶምነትን የማይቀበሉ ተብለው ግንቦት ሰባት፣ ኦነግና ብኦነግ እንደሚወነጀሉ አትጠራጠሩ።

እንደ ገና ዳቦ ከታችም ከላይም በወያኔ ውሸት ለሚጠበሰው ትግራይ ሕዝብ  የትግራይ ሙሁራን ካልቆሙ ማን ሊቆም  ነው።አቶ መኮንን ዘለለውና አቶ ገብረመድህን በትግራይ ክፍለሃገር በትግራይ ጎጀሌዎች የተፈጸመውን  ሰቆቃ ለቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለማሳየት ሞክረዋል። ሌሎችም በትግሉ አካባቢ የነበሩና የሕዝቡን ስቃይ የሚያውቁ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ኢፋ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። በጥቂቅ ኅጠኞች ምክንያት ለዘመናት አብሮ የኖረ ሕዝብ በውሸታሞች ስብከት ሲለያይ አቶ ዝም ማለት ከጥፋትኝነት አያድንም ። የቀረውም  የኢትዮጵያ ሕዝብ የወገኑን የትግራይ ሕዝብ ሰቆቃና አንገቱን የደፋበትን ምክንያት እስከ አላወቀ ድረሰ ጠላም ወደደም ተብሎ ሊወቀስ አይገባም ።ማወቅና  ማሳወቅ  የሁላችንም ግዴታ መሆን  አለበት። በኦሮመኛ ‘ኦዶ ኢሣ አዱሬን ሌንጫ’ ይባለል። ‘በቄዬው ድመትም ነብር ነው’ ማለት ነው። ሁላችንም ለፍትህ ለነፃነት ለሰው ልጅነት ክብር በያአለንበት በየቄያችን ለሕዝቦች አንድነት ቆሞ ማሳየትን  ከታላቁ መምህር ከኔሰው ገብሬ መማር አለብን! የኢትዮጵያ ሕዝብ ለከፋፋዮች በር አይከፍትም።

ታደለ መኩሪያ
tadele@shaw.ca